የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፲፪
አዲስ አበባ ጥር ፲፱ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No. 12
ADDIS ABABA 27th January, 2014


ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፰፻፲/፪ሺ፮ ዓ.ም


የኢነርጂ አዋጅ.........................ገጽ ፯ሺ፪፻፳፩


## አዋጅ ቁጥር ፰፻፲/፪ሺ፮

## ስለኢነርጂ የወጣ አዋጅ

ለአገሪቱ የተፋጠነ የኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገት ዋነኛ ከሆኑ ግብዓቶች ውስጥ ኢነርጂ አንዱ በመሆኑ፤

በሥራ ላይ ያለውን የኤሌክትሪክ አዋጅ ከወቅቱ ብሔራዊ እና አካባቢያዊ የኢነርጂ ቁጥጥር አሰራር እድገት አንጻር ማሻሻልና የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ቁጥጥርን በማካተት በአዲስ የኢነርጂ አዋጅ መተካት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የኢነርጂ አዋጅ ቁጥር ፰፻፲/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ:-

፩/ "ኢነርጂ" ማለት ከውሃ ኃይል፣ ከፀሐይ፣ ከነፋስ፣ ከከርሰ ምድር እንፋሎት ወይም ከሌላ ምንጭ የሚገኝ የኤሌክትሪክ ኃይል ነው፤

፪/ "ማመንጨት" ማለት ኤሌክትሪክ ማምረት ነው፤

፫/ "ማስተላለፍ" ማለት በከፍተኛ ቮልቴጅ የኤሌክትሪክ ኃይል ማጓጓዝ ነው፤

ያንዱ ዋጋ Unit Price 14.60

CONTENTS

Proclamation No. 810/2013


Energy Proclamation ......................... Page 7221


## PROCLAMATION No. 810/2013

## A PROCLAMATION ON ENERGY

WHEREAS, energy is one of the indispensable inputs necessary for accelerating the economic and social development of the country;

WHEREAS, the existing Electricity Proclamation needs to be revised based on the current national and regional development of energy regulations and be replaced by a new energy law that include regulations of both electricity and energy efficiency and conservation;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### PART ONE

### GENERAL

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Energy Proclamation No. 810/2013".

**2. Definitions**

In this Proclamation unless the context otherwise requires:

1/ "energy" means electric power generated from hydropower, solar, wind, geothermal or other sources;

2/ "generation" means the production of electricity;

3/ "transmission" means the transportation of electricity through high voltage lines;

፬/ "ማከፋፈል" ማለት በመካከለኛና በአነስተኛ ቮልቴጅ መስመሮች አማካይነት ለደንበኞች የሚቀርብ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ነው፤

፭/ "ግሪድ" ማለት የኤሌክትሪክ ኃይል ከማመንጫ ጣቢያ ተነስቶ ለደንበኞች የሚቀርብበት የማገናኛ ቦታዎችን ጨምሮ የተያያዘው የማስተላለፊያና ማከፋፈያ ሥርዓት ነው፤

፮/ "ዝቅተኛ ቮልቴጅ" ማለት እስከ ፬፻ ቮልት የሚደርስ የቮልቴጅ መጠን ነው፤

፯/ "መካከለኛ ቮልቴጅ" ማለት ከ፬፻ በላይ እስከ ፴፫ሺ ቮልት የሆነ የቮልቴጅ መጠን ነው፤

፰/ "ከፍተኛ ቮልቴጅ" ማለት ከ፴፫ሺ ቮልት በላይ የሆነ የቮልቴጅ መጠን ነው፤

፱/ "የኤሌክትሪክ ሥራ" ማለት የኤሌክትሪክ ዲዛይን፣ ኢንስታሌሽን፣ ጥገና፣ ፍተሻ፣ መቆጣጠር፣ ተቋራጭነት ወይም ማማከር፣ የኤሌክትሮሜካኒካል ሥራ ወይም ማንኛውም ሌላ ኤሌክትሪክ ነክ የንግድ ሥራ ነው፤

፲/ "ኢንስታሌሽን" ማለት ኤሌክትሪክን ከአቅርቦቱ አንስቶ ጥቅም ላይ እስከሚውልበት ቦታ ለማድረስ ጥቅም ላይ የዋሉ ወይም እንዲውሉ የተገጠሙ ሽቦዎችን፣ እቃዎችን፣ አያያዦችን እና ሌሎች ቁሳቁሶችን ያጠቃልላል፤

፲፩/ "ደንበኛ" ማለት ከባለፈቃድ የኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚያገኝ ሰው ነው፤

፲፪/ "ኮድ" ማለት በባለሥልጣኑ መመሪያ የተደነገጉ የኤሌክትሪክ ሥራዎችን ወይም የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃዎችን የሚመለከቱ የሥርዓቶችና የአሠራሮች ስብስብ ነው፤

፲፫/ "የኢነርጂ ኦዲት" ማለት፡-

ሀ) የአንድን ደንበኛ የኢነርጂ ፍጆታ አጠቃቀም በቂ እውቀት ለማግኘት፤

ለ) አዋጭ የሆኑ የኢነርጂ ቁጠባ እድሎችን ለመለየትና መጠናቸውን ለመለካት፤ እና

ሐ) ግኝቶቹን ሪፖርት ለማድረግ፤

የሚያስችል የተቀናጀ ሥርዓት ነው፤

፲፬/ "የኢነርጂ ቁጠባ" ማለት በአንድ ሂደት ወይም ሥርዓት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውለውን የኢነርጂ መጠን ብክነትን በማስወገድ እና ኢኮኖሚያዊና አግባብ በሆነ አጠቃቀም መቀነስ ነው፤

4/ "distribution" means the supply of electricity services to customers through medium and low voltage lines;

5/ "grid" means the network of transmission and distribution systems and connection points for the movement and supply of electrical energy from generating stations to customers;

6/ "low voltage" means a voltage of supply up to 400 volts;

7/ "medium voltage" means a voltage level above 400 up to 33,000 volts;

8/ "high voltage" means a voltage level above 33,000 volts;

9/ "electrical work" means a work of electrical design, installation, maintenance, testing, inspection, contracting or consultancy, electromechanical activity or any other electric related business;

10/ "installation" includes wirings, equipment, fittings and other materials used or intended to be used to convey electricity beyond the point of supply to the point of consumption;

11/ "customer" means a person obtaining electricity services from a licensee;

12/ "code" means an organized set of procedures and practices prescribed by the directive of the Authority to be applicable with respect to electrical works or service level standards;

13/ "energy audit" means a systematic procedure:

a) to obtain adequate knowledge of the existing energy consumption profile of a customer;

b) to identify and quantify cost effective energy saving opportunities; and

c) to report the findings;

14/ "energy conservation" means reduction in the amount of energy consumed in a process or system through elimination of waste and economical and rational use;

፲፭/ "የኢነርጂ ብቃት" ማለት በዝቅተኛ የኢነርጂ ፍጆታ ተመሳሳይ ወይም ከፍ ያለ ምርት ወይም አገልግሎት ማቅረብ መቻል ነው፤

፲፮/ "የኢነርጂ ብቃት ተለጣፊ ምልክት" ማለት ተጠቃሚዎች ግዢ በሚፈጽሙበት ወቅት ስለንብረቱ የኢነርጂ አጠቃቀም ብቃት እንዲያውቁ አስፈላጊውን ግንዛቤ ለመስጠት የሚያስችል መረጃን የያዘ በንብረቱ ላይ የሚለጠፍ ምልክት ነው፤

፲፯/ "የኢነርጂ አገልግሎት ኩባንያ" ማለት የደንበኛን መገልገያ ወይም ይዞታ በሚመለከት የኢነርጂ ብቃት ማሻሻያ አገልግሎት የሚሰጥና ለሰጠው አገልግሎትም ክፍያውን በሙሉ ወይም በከፊል በተገኘው የኃይል ብቃት መሻሻል ላይ ተመሥርቶ የሚቀበል ኩባንያ ነው፤

፲፰/ "የፈቃደኝነት ስምምነት" ማለት የኢነርጂ ብቃትን ለማሻሻል በሁሉም ተሳታፊ ወገኖች ስምምነት የተደረሰባቸው ኢላማዎች በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እንዲያከናውኑ ለማስቻል ግዴታዎችን የሚጥል ባለሥልጣኑ ከማንኛውም ሰው ጋር የሚያደርገው ውል ነው፤

፲፱/ "ፈንድ" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፫ መሠረት የተቋቋመው የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ፈንድ ነው፤

፳/ "ባለአደራ ወኪል" ማለት ከፈንዱ ልዩ ልዩ ምንጮች የሚሰበሰበውን ገንዘብ እንዲያስቀምጥ፣ በቦርዱም ትዕዛዝ ብድር እንዲሰጥና ተከፋይ ገንዘቡንም እንዲቀበል የተወከለ ማንኛውም የፋይናንስ ተቋም ነው፤

፳፩/ "ፈቃድ" ማለት ለንግድ ዓላማ ኤሌክትሪክ ለማመንጨት፣ ለማስተላለፍ፣ ለማሰራጨትና ለመሸጥ፣ ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት ወይም ወደ ውጭ አገር ለመላክ፣ ወይም የኢነርጂ ኦዲት፣ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ተቋራጭ ወይም የማማከር አገልግሎቶችን ለማከናወን በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

፳፪/ "ባለፈቃድ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤

፳፫/ "የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት" ማለት የኤሌክትሪክ ሥራዎች የማከናወን ብቃትን በማረጋገጥ ለማንኛውም ሰው በባለሥልጣኑ የሚሰጥ ሰነድ ነው፤

፳፬/ "ታሪፍ" ማለት ለኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚከፈል የዋጋ ተመን ዝርዝር ነው፤

15/ "energy efficiency" means the ability to provide the same or higher level of products or services at lower energy consumption;

16/ "energy efficiency label" means label affixed on energy consuming asset to describe the asset's energy performance in order to provide consumers the data necessary to make informed purchase;

17/ "energy service company" means a company that delivers energy efficiency improvement service with respect to a customer's facility or premises and accepts payment for the service based, either wholly or in part, on the achievement of energy efficiency improvement;

18/ "voluntary agreement" means a contract between the Authority and any person on agreed targets with commitments and time schedules on the part of all participating parties to improve energy efficiency;

19/ "Fund" means the Energy Efficiency and Conservation Fund established under Article 23 of this Proclamation;

20/ "trust agent" means any represented financial institution that keeps the money collected from various sources of the Fund as well as advances and collects loans upon the order of the Board;

21/ "license" means a license issued pursuant to this Proclamation to generate, transmit, distribute and sale, import or export electricity for commercial purposes; or to undertake energy audit, energy efficiency and conservation contracting or consultancy services;

22/ "licensee" means a person issued with a license pursuant to this Proclamation;

23/ "certificate of competency" means a document issued by the Authority that certify the competency of any person to engage in electrical works;

24/ "tariff" means the list of charges for electricity services;

፳፭/ "ባለሥልጣን" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የሚቋቋም የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን ነው፤

፳፮/ "ቦርድ" ማለት የባለሥልጣኑ ቦርድ ነው፤

፳፯/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯(፩) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤

፳፰/ "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፳፱/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል::

## ክፍል ሁለት

## የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን

### ፫. መቋቋም

የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይቋቋማል::

### ፬. የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

፩/ በዚህ አዋጅ እና በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦችና መመሪያች መሠረት ፈቃድና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠትና ማደስ፤

፪/ ማንኛውም ባለፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እና በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችንና መመሪያችን አክብሮ እየሠራ መሆኑን መቆጣጠር፤ ይህ አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ተጥሰው ሲገኙም እንደጥፋቱ ክብደት ባለፈቃዱን ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠውን ሰው በገንዘብ መቅጣት ወይም ፈቃዱን ማገድ ወይም መሠረዝ፤

፫/ በባለፈቃድ የሚቀርብለትን ከብሔራዊ ግሪዱ ጋር የተያያዘ ታሪፍ መገምገምና እንዲጸድቅ ለመንግስት የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ፤ ሲጸድቅም አፈጻጸሙን መቆጣጠር፤ ከብሔራዊ ግሪዱ ውጭ የሆኑ ታሪፎችን አወሳሰን መመሪያ ማውጣትና አፈጻጸሙን መቆጣጠር፤

25/ "Authority" means the Ethiopian Energy Authority to be established by the regulation of the Council of Ministers;

26/ "Board" means the Authority's Board;

27/ "region" means any state referred to in Article 47(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

28/ "person" means a natural or juridical person;

29/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## PART TWO

## THE ETHIOPIAN ENERGY AUTHORITY

### 3. Establishment

The Ethiopian Energy Authority shall be established by regulations to be issued by the Council of Ministers.

### 4. Powers and Duties of the Authority

The Authority shall have the powers and duties to:

1/ issue and renew license and certificate of competency in accordance with this Proclamation and regulations and directives issued hereunder;

2/ supervise the operations of licensees and holders of certificates of competency to ensure compliance with the provisions of this Proclamation and regulations and directives issued hereunder; and in the case of contravention of this Proclamation or regulations or directives issued hereunder, penalize the licensee or the holder of a certificate of competency with fine or suspend or revoke his license or certificate of competency, depending on the gravity of the offence;

3/ review national grid related tariff submitted to it by a licensee and submit its recommendation to the government for approval; and, upon approval, regulate the implementations thereof; issue and regulate the implementation of guidelines for the determination of off-national-grid tariffs;

፬/ የረጅም፣ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ስትራቴጂና ፕሮግራም በአገር አቀፍ እንዲሁም በዘርፍ ደረጃ ማዘጋጀት እና አፈጻጸማቸውን በየወቅቱ በሚቀርቡለት ሪፖርቶች መሠረት መገምገም፤

፭/ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባን በብሔራዊ እና በዘርፍ ደረጃ ማስፋፋት፤

፮/ የኢነርጂ ኦዲት ኮድ፣ የኢነርጂ ብቃት ደረጃዎች ኮድ፣ የኢነርጂ ብቃት ማረጋገጫ ተለጣፊ ምልክት ኮድ፣ የግሪድ ኮድ፣ የደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ ኮድ፣ የኢንስፔክሽን ኮድ፣ የአገልግሎት ጥራት ደረጃ ኮድ፣ የሕንፃ ኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ ኮድ፣ የቴክኒካል ስታንዳርድ ኮድ እና ሌሎች ኮዶችን ማውጣት እና አፈጻጸማቸውንም መቆጣጠር፤

፯/ የኤሌክትሪክ ኃይል ግዢ እና የኔትወርክ አገልግሎት ስምምነቶችን ማጽደቅ፤

፰/ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባን፣ የኢነርጂ ልማትን እና የኤሌክትሪክ ኃይል ንግድን ለማስፋፋት ከሥልጠና ተቋማት እና ከአህጉራዊና ከዓለም አቀፍ መድረኮች ጋር መተባበር፤

፱/ የኢነርጂ ብቃት መፈተሻ ላብራቶሪዎችን ማቋቋም እና የፍተሻ ሥርዓቶችን ማውጣትና መተግበር፤

፲/ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ጥናትን፣ ልማትንና ሠርቶ ማሳያን እንዲሁም የቴክኖሎጂ ዝውውር ተግባራትን ማስፋፋትና ማስተባበር፤

፲፩/ ከኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ጋር የተዛመዱ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መተንተን፣ ማደራጀትና ማሰራጨት፤

፲፪/ በዚህ አዋጅ መሠረት ቁጥጥር ሊደረግበት በሚገባ በማናቸውም ጉዳይ ላይ በሚመለከታቸው ወገኖች መካከል አለመግባባት በመከሰቱ የቀረበ አቤቱታን መስማት፣ ማጣራት እና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም ማስማማት ወይም በግልግል መጨረስ፤

፲፫/ በአዋጁ መሠረት በሚወጣ ደንብ የሚወሰኑ ፈቃድና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለመስጠትና ለማደስ እና ለሚሰጣቸው ሌሎች አገልግሎቶች የሚጠየቁ ክፍያዎችን እና የፈንዱን ገቢዎች መሰብሰብ፤

፲፬/ እንደአስፈላጊነቱ ሥልጣንና ተግባሩን አግባብ ላላቸው የክልል አስፈጻሚ አካላት በውክልና ማስተላለፍና የአቅም ግንባታ ድጋፍ መስጠት፡፡

4/ formulate long-term, medium-term, and short-term energy efficiency and conservation strategy and program at national and sectoral levels and, on the basis of periodic reports to be submitted to it, evaluate the implementations of same;

5/ promote energy efficiency and conservation at national and sectoral levels;

6/ issue energy audit code, energy efficiency standards code, energy efficiency labeling code, grid code, customers' service code, technical inspection code, quality service standard code, building electrical installation code, technical standard code and other codes; and supervise the implementations of same;

7/ approve electric power purchase and network service agreements;

8/ cooperate with training institutions and regional and international forums for promoting energy efficiency and conservation, energy development and power trade;

9/ establish energy efficiency testing laboratories and issue and implement testing procedures;

10/ promote and coordinate energy efficiency and conservation research, development and demonstration and technology transfer activities;

11/ collect, analyze, organize and disseminate information relating to energy efficiency and conservation;

12/ hear, investigate and, when necessary, mediate or arbitrate disputes between parties with complaint over any matter required to be regulated under this Proclamation;

13/ collect fees for the issuance and renewal of licenses and certificates of competency and for other services it renders and the revenues of the Fund, in accordance with the regulation to be issued hereunder;

14/ where necessary, delegate its powers and duties to the appropriate regional executive organs and provide them with capacity building support.

## ፭. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

፩/ ከብሔራዊ ግሪድ ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ የታሪፍ የውሳኔ ሃሳቦችን መርምሮ እንዲጸድቁ ለመንግሥት ያቀርባል፤

፪/ ከብሔራዊ ግሪዱ ውጭ የሆኑ ታሪፎች አወሳሰን መመሪያን፣ ብሔራዊ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ስትራቴጂንና ፕሮግራምን እና የኤሌክትሪክ ኃይል ግዢና የኔትወርክ አገልግሎት ስምምነቶችን ያጸድቃል፤

፫/ በዚህ አዋጅ መሠረት ባለሥልጣኑ የሚያወጣቸውን መመሪያዎች ያጸድቃል፤

፬/ ፈንዱ በወቅቱ መሰብሰቡንና በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፤

፭/ የባለአደራ ወኪል ምርጫን እንደሁም ከፈንዱ የሚሰጡ ብድሮችን ያጸድቃል።

## ክፍል ሦስት

## ስለፈቃድ እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

## ፮. የፈቃድ አስፈላጊነት

፩/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ መሰረት ፈቃድ ሳይኖረው ለንግድ ዓላማ ኤሌክትሪክ ማመንጨት፣ ማስተላለፍ፣ ማከፋፈልና መሸጥ፣ ወደ ውጭ አገር መላክ ወይም ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ወይም የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ማማከር፣ የኢነርጂ አገልግሎት ተቋራጭነት፣ የኢነርጂ ኦዲት ወይም ከእነዚህ ሥራዎች ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን መስራት አይችልም።

፪/ ለንግድ ላልሆነ ዓላማ ኤሌክትሪክ ለማመንጨት፣ ለማስተላለፍ ወይም ለማከፋፈል ፍላጎት ያለው ማንኛውም ሰው በቅድሚያ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ እና የአካባቢ ጥበቃና የአደጋ መከላከያ ሁኔታዎችን ማሟላቱን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ መረጃዎችን ማቅረብ አለበት።

፫/ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ኤሌክትሪክ በማመንጨት፣ በማስተላለፍ፣ በማከፋፈልና መሸጥ፣ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባን በማማከር፣ የኢነርጂ አገልግሎት ተቋራጭነት፣ የኢነርጂ ኦዲት ወይም ሌሎች ከዚህ አዋጅ ጋር የተያያዙ ተግባራትን ሲያከናውን የነበረ ማንኛውም ሰው አስፈላጊ የሆኑ ዝርዝር መረጃዎችን የያዘ ማመልከቻ ለባለሥልጣኑ በማቅረብ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል።

## 5. Powers and Duties of the Board

Without prejudice to other provisions of this Proclamation, the Board shall have the powers and duties to:

1/ review tariff proposals in relation to the national grid and submit same to the government for approval;

2/ approve off-national-grid tariffs determination guidelines, national energy efficiency and conservation strategy and program, model power purchase and network service agreements;

3/ approve directives of the Authority to be issued pursuant to this Proclamation;

4/ ensure the timely collection of the Fund and its proper utilization;

5/ approve the selection of a trust agent and grants of loans from the Fund.

## PART THREE

## LICENSE AND CERTIFICATE OF COMPETENCY

## 6. Requirements of License

1/ No person may generate, transmit, distribute and sale, import or export electricity for commercial purposes or engage in energy efficiency and conservation consulting, energy service contracting, energy audit or in other related activities without having a license in accordance with this Proclamation and the regulation to be issued hereunder.

2/ Any person desiring to generate, transmit or distribute electricity for non-commercial purposes shall notify the Authority in advance and produce documents evidencing that he has fulfilled environmental protection and safety conditions.

3/ Any person who has engaged in the generation, transmission, distribution and sale of electricity, energy efficiency and conservation consulting, energy service contracting, energy audit or in any other activities related to this Proclamation prior to the coming into force of this Proclamation shall be required to submit to the Authority an application, along with necessary particulars, and obtain a license.

## ፯. ፌቃድ ለማግኘት ብቁ ስለመሆን

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ እና በአዋጁ መሰረት በሚወጣ ደንብ፣ በኢንቨስትመንት እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተገለጹትን ፈቃድ ለማግኘት ብቁ የሚያደረጉ መስፈርቶችን ካሟላ፣ በንግድ ሕግ መሠረት የንግድ ሥራ ማካሄድ የሚችል እንዲሁም የፈቃድ ግዴታዎችን ለመወጣት የሚያስችል የገንዘብ ምንጭ፣ የቴክኒክ ችሎታ፣ ሙያ እና ልምድ ያለው መሆኑ በባለሥልጣኑ ሲረጋገጥ ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

## ፰. ፌቃድን ስለማደስ፣ ስለማገድ እና ስለመሰረዝ

፩/ ፈቃድ እንዲታደስለት የሚያመለክት ማንኛውም ባለፈቃድ በዚህ አዋጅና በአዋጁ መሰረት በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተመለከቱትን መስፈርቶች አሟልቶ መቅረብ አለበት፡፡

፪/ ባለፈቃዱ በዚህ አዋጅ፣ በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ወይም በፈቃዱ ላይ የተጠቀሱትን ግዴታዎች ካላከበረ ባለሥልጣኑ በገንዘብ ሊቀጣው ወይም ፈቃዱን ሊያግድ ወይም ሊሰርዝ ይችላል፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ ፈቃድ ከመሰረዙ በፊት ባለፈቃዱ ስህተቱን እንዲያርም በቂ ይሆናል ብሎ የሚገምተውን ጊዜ ይሰጠዋል፡፡

፬/ የወራሾች መብት እንደተጠበቀ ሆኖ እንደአግባብነቱ ባለፈቃዱ ሲሞት ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከሆነ ሲፈርስ ወይም አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የመክሰር ውሳኔ ሲሰጥበት ፈቃዱ ሊሰረዝ ይችላል፡፡

## ፱. ፌቃድን ስለማስተላለፍና ምትክ ፌቃድ ስለመስጠት

፩/ በባለሥልጣኑ የተሰጠ ማናቸውም ፈቃድ በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም በወጣ ደንብ መሠረት በባለሥልጣኑ የጽሑፍ ስምምነት ለሌላ ሰው ሊተላለፍ ይችላል፡፡

፪/ የማመንጨት፣ የማስተላለፍ፣ የማከፋፈልና የመሸጥ፣ ወደ አገር ውስጥ የማስገባት ወይም ወደ ውጭ አገር የመላክ ባለፈቃድ የንግድ ሥራው በዋስትና በመያዙ፣ በመተላለፉ ወይም ከሌላ ጋር በመቀላቀሉ ምክንያት በመቆጣጠር ወይም በባለቤትነት መብቱ ላይ ለውጥ ሲደረግ በባለሥልጣኑ መጽደቅ ይኖርበታል፡፡

## 7. Eligibility for License

Any person shall be issued with a license where the Authority is satisfied that he meets the requirements of the license specified in this Proclamation, regulation to be issued hereunder and the investment and other relevant laws, qualifies to carry on trade under the Commercial Code, and has the financial resources, technical competence, professional skill and experience required to fulfill the license obligations.

## 8. Renewal, Suspension and Revocation of License

1/ Any licensee applying for renewal of a license shall fulfill the requirements of this Proclamation and regulations and directives issued hereunder.

2/ The Authority may impose fine or suspend or revoke a license where the licensee fails to comply with obligations specified in this Proclamation, regulations or directives issued hereunder or in the license.

3/ Prior to revocation of a license the Authority shall give the licensee reasonable time as it deems sufficient to remedy failures.

4/ Without prejudice to the rights of heirs, a license may be revoked, as the case may be, upon the death of the licensee or upon liquidation or declaration of bankruptcy under the relevant law, in the case of a juridical person.

## 9. Transfer and Replacement of License

1/ Any license issued by the Authority may be transferred to another person with the written consent of the Authority in accordance with this Proclamation and regulation issued hereunder.

2/ Any change in the control or ownership right of a generation, transmission, distribution and sale, import or export licensee shall be approved by the Authority where that change comes by mortgaging, transferring or merger of the business of the licensee.

፫/ ማናቸውንም የባለፈቃዱን የማይንቀሳቀስ ንብረት ወይም ከሃያ አምስት በመቶ በላይ የሆነን የአክስዮን ድርሻ የሚመለከት ሽያጭ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተገለጸው መሠረት በመቆጣጠር ወይም በባለቤትነት መብት ላይ ለውጥ እንደተደረገ ያስቆጥራል፡፡

፬/ ፈቃዱ የጠፋበት ወይም የተበላሸበት ባለፈቃድ ምትክ ፈቃድ እንዲሰጠው ሲያመለክት በዚህ አዋጅ መሠረት በወጣ ደንብ የተወሰነውን ክፍያ በማስከፈል ምትክ ፈቃዱ ሊሰጠው ይችላል፡፡

## ፲. የባለፈቃድ ግዴታዎች

፩/ ማንኛውም ባለፈቃድ:-

ሀ/ በዚህ አዋጅ መሰረት በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት ስለ ሥራው አግባብነት ያላቸውን ሪከርዶች ይይዛል፤ እንዲሁም እቅዶችን፣ ሪፖርቶችን፣ መረጃ ዎችንና ደጋፊ ማስረጃዎችን ለባለ ሥልጣኑ ያቀርባል፤

ለ) መዛግብቱና ሪከርዶቹ በአግባቡ ሥልጣን በተሰጣቸው የባለሥልጣኑ ሃላፊዎች እንዲመረመሩ ሲጠየቅ ለምርመራ ያቀርባል፡፡

፪/ ማንኛውም ባለፈቃድ ሥራዎቹን ሲያከናውን ይህን አዋጅ፣ በአዋጁ መሰረት የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን እና አግባብነት ያላቸውን የአካባቢ ጥበቃ ሕጎችን እንዲሁም በባለሥልጣኑ የተወሰኑትን የጥንቃቄ፣ የጥራትና የአተገባበር ደረጃዎችን ማክበር አለበት፡፡

፫/ ኤሌክትሪክ በማመንጨት፣ በማስተላለፍ፣ በማከፋፈልና መሸጥ፣ ወደ አገር ውስጥ በማስገባት ወይም ወደ ውጭ አገር በመላክ ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ባለፈቃድ ፈቃዱን ከወሰደበት ጊዜ ጀምሮ በአስራ ሁለት ወራት ውስጥ ሥራውን መጀመርና ሥራውን ስለመጀመሩም ለባለሥልጣኑ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

## ፲፩. ስለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

፩/ የኤሌክትሪክ ሥራ ተግባራትን ማከናወን የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ መሠረት በባለሥልጣኑ የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ከባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የወሰደ ማንኛውም ሰው ሥራ ከመጀመሩ በፊት እንደአግባብነቱ ከፌደራል ንግድ ሚኒስቴር ወይም ከክልል ንግድ ቢሮ ተገቢውን የንግድ ፈቃድ ማውጣት ይኖርበታል፡፡

3/ A change in control or ownership by sale stated under the provisions of sub-article (2) of this Article shall include a sale of any of the fixed assets or over 25% of the shares of the licensee.

4/ Any licensee whose license has been lost or damaged may be issued with a replacement license upon application and payment of the required fees determined by regulation issued hereunder.

## 10. Obligations of Licensee

1/ Any licensee shall:

a) keep relevant records of operations, and submit plans, reports, information and supporting documents to the Authority in accordance with regulations and directives issued hereunder;

b) make books and records of operation available for inspection when requested by duly authorized officials of the Authority.

2/ Any licensee shall carry out his activities in compliance with this Proclamation, regulations and directives issued hereunder and in the relevant environmental protection laws, and safety, quality and performance standards determined by the Authority.

3/ Any licensee engaged in the generation transmission, distribution and sale, impor or export of electricity shall commence operation within twelve months from th date of issuance of license, and report to th Authority about its commencement.

## 11. Certificate of Competency

1/ Any person who wants to undertak electrical work activities shall obtain certificate of competency in accordanc with this Proclamation and regulation to b issued hereunder.

2/ Any person which has been issued with certificate of competency in accordanc with sub-article (1) of this Article sha prior to commencement of operation, obta the appropriate trade license from tl Ministry of Trade or a regional trade burea as the case may be.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ከባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የወሰደ ማንኛውም ግለሰብ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ለማሳደስ ሲፈልግ በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣ ደንብ የሚገለጸውን አግባብነት ያለውን የሥራ ልምድ ወይም የተከታታይ ትምህርት ፕሮግራም ተሳትፎ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል።

፬/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለመስጠት፣ ለማደስ፣ ለማገድ፣ ለመሰረዝ ወይም ምትክ ለመስጠት መሟላት የሚኖርባቸው መስፈርቶችና ሁኔታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ ይወሰናሉ።

## ክፍል አራት

## የኤሌክትሪክ አቅርቦት ተግባራትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች

**፲፪. ባለፈቃዱ የኤሌክትሪክ አገልግሎቶችን የሚያቋርጥባቸው ሁኔታዎች**

፩/ ባለፈቃዱ በሚከተሉት ምክንያቶች ካልሆነ በስተቀር የኤሌክትሪክ አገልግሎቶችን ሊያቋርጥ አይችልም:-

ሀ) የኤሌክትሪክ እቃዎችን ወይም መስመሮችን ለመፈተሽ፣ ለመጠገን፣ ለማደስ፣ ለማስተካከል ወይም ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች አስፈላጊ ሥራዎችን ለማከናወን፤

ለ) እንደ ውሃ ሙላት፣ የመሬት መናድና መንቀጥቀጥ ያሉ ወይም ከባለፈቃዱ አቅም በላይ የሆኑ ሌሎች የተፈጥሮ አደጋዎች ሲከሰቱ፤

ሐ) ደንበኛው ክፍያ ሳይፈጽም ሲቀር፤

መ) ደንበኛው ስምምነት ካደረገበት ግዴታዎች እና ሁኔታዎች ውጪ ያልተፈቀደለትን ኤሌክትሪክ ሲጠቀም ወይም የገባለትን የኤሌክትሪክ ቆጣሪ ሲያስናክል።

፪/ ባለፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ሀ) በተደነገገው መሰረት የኤሌክትሪክ አገልግሎቱን ከማቋረጡ አስቀድሞ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው ደንብ በተገለጸው ጊዜ ውስጥ ለህብረተሰቡ ማስታወቅ አለበት።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ለ)፣ (ሐ) እና (መ) የተመለከቱት ሁኔታዎች እንደተስተካከሉ ባለፈቃዱ የኤሌክትሪክ አገልግሎቱን ወዲያውኑ መቀጠል አለበት።

3/ Any individual who wants to renew a certificate of competency issued in accordance with sub-article (1) of this Article shall produce evidence showing the relevant work experience or participation in a continuing education program as specified by regulation to be issued hereunder.

4/ The requirements and conditions for the issuance, renewal, suspension, revocation or replacement of a certificate of competency shall be prescribed by regulation to be issued hereunder.

## PART FOUR

## PROVISIONS RELATING TO ELECTRICITY SUPPLY ACTIVITIES

**12. Conditions for Interruption of Electricity Services by the Licensee**

1/ A licensee may not interrupt electricity services except for the following reasons:

a) to inspect, repair, maintain, adjust or to undertake other necessary works related to electrical equipment or lines;

b) where natural calamities such as floods, landslides, earthquakes or other events beyond the control of the licensee occur;

c) where a customer fails to pay charges;

d) where a customer utilizes unauthorized electricity contrary to the terms and conditions agreed up on, or tamper with electricity meter installed.

2/ The licensee shall notify the general public in advance of interrupting electricity services as provided under sub-article (1)(a) of this Article within the time limit specified in regulation to be issued hereunder.

3/ The licensee shall resume supplying electricity services as soon as the conditions stated under sub article (1) (b), (c) and (d) of this Article are rectified.

**፲፫. ብሔራዊ ግሪድ**

፩/ መንግስት ማንኛውንም የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ መስመር በማስታወቂያ ብሔራዊ ግሪድ ብሎ ለመሰየም ይችላል::

፪/ በብሔራዊ ግሪዱ መጠቀም የሚቻልበት አግባብ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ መሰረት ይሆናል::

**፲፬. የኤሌክትሪክ ኃይል ንግድ**

፩/ የኤሌክትሪክ ኃይል ወደ አገር ውስጥ የሚገባበት ወይም ወደ ውጭ አገር የሚላክበት ሁኔታ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል::

፪/ የኃይል ግዢ ስምምነት ሳይኖር የኤሌክትሪክ ኃይል ንግድ የሚከናወንበት አግባብ በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል::

**፲፭. ስለመቆጣጠር**

፩/ በባለሥልጣኑ የተወከለ ሃላፊ ለህሊና ግምት ተገቢ በሆነ በማናቸውም ሰዓት የኤሌክትሪክ ማመንጨት፣ ማስተላለፍ፣ ማከፋፈልና መሸጥ ወይም የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽ ሥራዎችን ሳያግድ ወይም ሳያደናቅፍ በቦታው ውስጥ በመግባት መመርመር ወይም መቆጣጠር ይችላል::

፪/ ማናቸውም የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን የደህንነት መስፈርትን ስለማሟላቱ ፈቃድ ባለው የኤሌክትሪክ ተቆጣጣሪ ሳይረጋገጥ ከባለፈቃዱ የኤሌክትሪክ አቅርቦት መስመር ጋር ማገናኘት አይቻልም::

## ክፍል አምስት

## ለኤሌክትሪክ አቅርቦት ሥራዎች በመሬት ስለመጠቀም

**፲፮. በመሬት ስለመጠቀም**

ማንኛውም የማመንጨት፣ የማስተላለፍ፣ የማከፋፈል፣ የመሸጥ፣ ወደ አገር ውስጥ የማስገባት ወይም ወደ ውጭ አገር የመላክ ባለፈቃድ:-

፩/ በማንኛውም ሰው ይዞታ ሥር ወደ ሆነ መሬት ወይም ቅጥር ግቢ በመግባት አዲስ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን መዘርጋት የሚችለው በቅድሚያ ከባለይዞታው ፈቃድ በማግኘት ነው፤

**13. National Grid**

1/ The government may, by notification, specify any transmission line as national grid.

2/ Conditions of access to the national grid shall be specified by regulation to be issued hereunder.

**14. The Electricity Trade**

1/ Conditions of importation or exportation of electricity shall be determined by regulation to be issued hereunder.

2/ Conditions of conducting electricity trade without the need for power purchase agreement shall be determined by regulation to be issued hereunder.

**15. Inspection**

1/ An officer duly authorized by the Authority may, at all reasonable time, enter premises and inspect or supervise the generation transmission, distribution and sale o electricity or electrical installation withou unreasonably impeding or obstructing activities thereof.

2/ No electrical installation may be energized from the supply line of the licensee withou being certified for safety compliance by a licensed electrical inspector.

## PART FIVE

## USE OF LAND FOR ELECTRICITY SUPPLY ACTIVITIES

**16. Use of Land**

Any generation, transmission or distribution an sale, import or export licensee:

1/ may enter the land or the premises in th holding of any person after securing pri permission from the person to carry o installation of new electricity supply;

፪/ በማንኛውም ሰው ይዞታ ሥር ወደ ሆነ መሬት ወይም ቅጥር ግቢ በመግባት የኤሌክትሪክ መስመር ለማገናኘት፣ ለመጠገን፣ ለማሻሻል፣ ለመመርመር ወይም መስመሩን ለማንሳት የሚያስፈልጉ ተግባራትን ለማከናወን የሚችለው በቅድሚያ ባለይዞታውን በማሳወቅ ነው፤

፫/ የኤሌክትሪክ ግንባታ ሥራዎችን ለማካሄድ መሰናከል የሚሆኑ ወይም በኤሌክትሪክ መስመር ላይ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ዛፎችን የመቁረጥ ወይም የመመልመል ወይም ሰብሎችን፣ አትክልቶችን ወይም ሌሎች ነገሮችን የማስወገድ መብት አለው።

**፲፯. ካሣ ስለመክፈል**

ባለፈቃዱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ የተደነገጉትን ተግባራት ሲያከናውን በባለይዞታው ንብረት ላይ ላደረሰው ጉዳት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ካሣ የመክፈል ግዴታ አለበት።

**፲፰. መሬትን ስለመውሰድ**

ማንኛውም የማመንጨት፣ የማስተላለፍ፣ የማከፋፈል እና የመሸጥ፣ ወደ አገር ውስጥ የማስገባት ወይም ወደ ውጭ አገር የመላክ ባለፈቃድ መንግሥት ለሕዝብ ጥቅም ሲባል አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ከግል ባለይዞታ የወሰደው መሬት ተጠቃሚ ሊደረግ ይችላል።

## ክፍል ስድስት

## የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች

**፲፱. የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ተግባራትን መቆጣጠር**

፩/ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ቁጥጥር ተግባራት በኢንዱስትሪና በሕንጻ ዘርፎች እና በኤሌክትሪክ እቃዎችና መገልገያ ቴክኖሎጂዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

፪/ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ተግባራት ቁጥጥር እንደአስፈላጊነቱ ከሚከተሉት አንዱን ወይም ከዚያ በላይ የሆኑትን ተግባራዊ በማድረግ ሊፈጸም ይችላል፦

ሀ) ዝቅተኛ የኢነርጂ ብቃት ደረጃን፤

ለ) የኢነርጂ ብቃት ተለጣፊ ምልክት ኮዶችን፤

ሐ) አስገዳጅ የኢነርጂ ኦዲትን፤

መ) የፈቃደኝነት ስምምነትን፤

ሠ) አስገዳጅ የኢነርጂ ቁጠባን፤ ወይም

ረ) አስገዳጅ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ እቃ ማስገጠምን።

2/ may enter the land or premises in the holding of any person after notifying that person to carry out activities required to connect, repair, upgrade, inspect or remove electrical lines;

3/ shall have the right to cut or lop trees or to remove crops, plants or other things that obstruct the construction or operation of electrical works or may cause danger to electrical lines.

**17. Compensation**

The licensee shall pay compensation, in accordance with the relevant law, for damages caused to the property of a landholder while performing the activities provided under Article 16 of this Proclamation.

**18. Expropriation of Land**

Where public interest so justifies, any generation, transmission, distribution and sale, import or export licensee may be made the beneficiary of an expropriation measure, taken in accordance with the relevant law, by the government over private land holdings.

## PART SIX

## PROVISIONS RELATING TO ENERGY EFFICIENCY AND CONSERVATION

**19. Regulating Energy Efficiency And Conservation Activities**

1/ Energy efficiency and conservation regulatory activities shall be applied to industry and building and technologies related to electrical equipment and appliance.

2/ Energy efficiency and conservation activity may be regulated through the application of any one or more of the following, as may be appropriate:

a) minimum energy efficiency standard;

b) energy efficiency labeling codes;

c) mandatory energy audit;

d) voluntary agreement;

e) mandatory energy saving; or

f) mandatory installation of energy efficient and conserving equipment.

፫/ ባለሥልጣኑ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ተግባራት ቁጥጥርን በራሱ ወይም ፈቃድ ባለው የኢነርጂ አገልግሎት ድርጅት አማካይነት ሊያከናውን ይችላል።

፬/ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው ደንብ መሰረት ከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚዎች የራሳቸውን የኢነርጂ አስተዳደር ክፍል እንዲያቋቁሙና በየወቅቱም ሪፖርት እንዲያቀርቡ ሊያስገድዳቸው ይችላል።

፭/ ባለሥልጣኑ በኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ከፍተኛ የአፈጻጸም ደረጃ ለማግኘት እንዲያስችለው ከኢነርጂ መገልገያ እቃ አምራቾች፣ አስመጪዎች ወይም ከከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚዎች ጋር ውጤቱ የሚለካና አስገዳጅነት ያለው የፈቃደኝነት ስምምነት መግባት ይችላል።

## ፳. ብሔራዊ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች

፩/ ባለሥልጣኑ ብሔራዊ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ስትራቴጂዎችንና ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ ያደርጋል።

፪/ ብሔራዊ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች በዝርዝር ኢኮኖሚያዊ የግምገማ ዓላማዎችና በሚለኩ ግቦች የተደገፉ መሆን አለባቸው።

፫/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሱትን ብሔራዊ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ስትራቴጂዎችንና ፕሮግራሞችን በየወቅቱ ይገመግማል።

## ፳፩. ስለሪፖርት አቀራረብ

፩/ ማንኛውም የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ አፈጻጸም ሪፖርት አስፈላጊ የሆኑ ስታንዳርዶችን መከተል እና የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ተግባሩ ሊፈጽመው የታሰበውን ሁሉንም ጉዳዮችን መያዝ እንዲሁም በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ የተመለከቱትን የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓቶችን መከተል ይኖርበታል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚቀርበው ሪፖርት ባለሥልጣኑ ስለኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ አሰራር ተገቢ ግንዛቤ እንዲያገኝ የሚያስችለው መሆን አለበት።

3/ The Authority may regulate energy efficiency and conservation activities on its own or through licensed energy service company.

4/ The Authority may oblige large energy consumers to establish their own energy management unit and submit periodic reports to the Authority as provided under regulation to be issued hereunder.

5/ The Authority may, in view of achieving higher level of performance in energy efficiency and conservation, enter into a voluntary agreement the result of which shall be measurable and binding with energy utilization equipment producers, importers or large-scale energy users.

## 20. National Energy Efficiency And Conservation Strategies and Programs

1/ The Authority shall develop and implement national energy efficiency and conservation strategies and programs.

2/ The national energy efficiency and conservation strategies and programs shall be accompanied by detailed economic evaluation objectives and measurable targets.

3/ The Authority shall review periodically the national energy efficiency and conservation strategies and programs mentioned under sub-article (1) of this Article.

## 21. Reporting

1/ Every energy efficiency and conservation performance report shall follow the necessary standards and contain all the required elements that the energy efficiency and conservation activity intended to accomplish and follow the reporting procedures as provided under regulation to be issued hereunder.

2/ The report submitted pursuant to sub-article (1) of this Article shall enable the Authority to take due account of the existing practice.

## ፳፪. የፈቃደኝነት ስምምነት

፩/ የፈቃደኝነት ስምምነቶች ግልጽና የማያሻማ ዓላማዎች እንዲሁም ዓላማዎቹም የማይፈጸሙ ወይም ሊፈጸሙ የማይችሉ በሚሆንበት ጊዜ ወደ ተሻሻሉ ወይም ወደ ተጨማሪ እርምጃዎች ሊመሩ የሚያስችሉ ከክትትልና ከሪፖርት አቀራረብ መስፈርቶች ጋር የተያያዙ ሥርዓቶች ሊኖሩዋቸው ይገባል፡፡

፪/ ግልጽነትን ከማረጋገጥ አንጻር የፈቃደኝነት ስምምነቶች ተግባራዊ ከመሆናቸው በፊት ሚስጥራዊ ድንጋጌዎች እስከፈቀዱ ድረስ ለህብረተሰቡ ሊደርሱ እና ሊታተሙ እንዲሁም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላትም አስተያየት እንዲሰጡባቸው የሚጋብዙ መሆን አለባቸው፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ በብሔራዊ ደረጃ የኢነርጂ ብቃትን የሚያበረታታ የፈቃደኝነት ስምምነት ተግባራዊ እንዲሆን የሚያስችል ፕሮግራም ቀርጾ ሊተገብር ይችላል፡፡

፬/ የፈቃደኝነት ስምምነት ለመግባትና የኢነርጂ ብክነቱን በተቀመጠው ግዴታና የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ለመቀነስ ፈቃደኛ ያልሆነ ማንኛውም የከፍተኛ ኢነርጂ ተጠቃሚ ደንበኛ ለሚያስከትለው የኢነርጂ ብክነት በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣ ደንብ የሚወሰነውን ክፍያ እንዲፈጽም ይደረጋል፡፡

## ፳፫. የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ፈንድ

፩/ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ፈንድ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ፈንዱ በኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ተግባር ላይ ለተሠማሩ ሰዎች ብድርና ድጋፍ ለመስጠት ዓላማ ይውላል፡፡

፫/ ፈንዱ የሚከተሉት የገንዘብ ምንጮች ይኖሩታል፦

ሀ) በመንግሥት የሚመደብ በጀት፣

ለ) ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት የሚገኝ ብድር እና ስጦታ፣

ሐ) መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የሚገኝ ስጦታ፣

መ) የኢነርጂ ብቃት ከሌላቸው የኤሌክትሪክ እቃዎችና መገልገያዎች፣ ሕንጻዎች እና ኢንዱስትሪዎች ከሚሰበሰብ መቀጮ፣ እና

ሠ) ከሌሎች ምንጮች የሚገኙ ገቢዎች፡፡

## 22. Voluntary Agreement

1/ Voluntary agreements shall have clear an unambiguous objectives, and monitorin and reporting requirements linked t procedures that can lead to revised o additional measures when the objectives ar not achieved or are not likely to b achieved.

2/ With a view to ensure transparency voluntary agreements shall be mad available to the public and published prio to application to the extent that applicabl confidentiality provisions allow and invit stakeholders' comment.

3/ The Authority may devise and implemen programs at national level that promot energy efficiency through the application o voluntary agreements.

4/ Any high energy consuming customer who refuses to conclude voluntary agreement and thereby reduce the energy loss based on the obligation and time schedule provided thereunder shall be obliged to pay the consequent energy loss charges as determined by regulation to be issued hereunder.

## 23. Energy Efficiency and Conservation Fund

1/ Energy Efficiency and Conservation Fund is hereby established.

2/ The Fund shall be utilized for the purpose of providing loans and financial supports to persons involved in energy efficiency and conservation activities.

3/ The sources of the Fund shall be:

a) budget allocated by the government;

b) loans and grants from international financial institutions;

c) grants from non-governmental organizations;

d) infraction from energy inefficient electrical equipment and appliances, buildings and industries; and

e) incomes from other sources.

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫)(መ) መሠረት የሚሰበሰበው የፈንዱ ገቢ በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

4/ Collection of the Fund as provided under sub-article (3)(d) of this Article shall be determined by regulation to be issued hereunder.

## ክፍል ሰባት

## የወንጀል ጥፋቶች እና ቅጣቶች

## PART SEVEN

## CRIMINAL OFFENCES AND PENALTIES

### ፳፬. ፈቃድ ሳይኖር ስለመስራት

በሌላ ሕግ ለህብረት ሥራ ማህበራት የተሰጠው መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ፈቃድ ሳይኖረው ለንግድ ዓላማ ኤሌክትሪክ ያመነጨ፣ ያስተላለፈ፣ ያከፋፈለና የሸጠ፣ ወደ አገር ውስጥ ያስገባ ወይም ወደ ውጭ አገር የላከ ወይም የኤሌክትሪክ ሥራን፣ ኢነርጂ ኦዲትን፣ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ የተቋራጭነት ወይም የማማከር አገልግሎትን ያከናወነ ማንኛውም ሰው እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ወይም እስከ ብር ፶ሺ. በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፤ አገልግሎት ሲሰጥባቸው የተገኙ ዕቃችና መገልገያዎችም በመንግስት ይወረሳሉ፡፡

### 24. Working Without Having License

Without prejudice the privileges provided to cooperative societies by other laws, any person who generates, transmits, distributes and sales, imports or exports electricity for commercial purposes, or perform electrical work, energy audit, energy efficiency and conservation contracting or consultancy service without having license shall be punished with rigorous imprisonment up to ten years or with a fine up to Birr 50,000 or with both, and forfeit his working equipment and appliances to the government.

### ፳፭. ከብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ጋር የተያያዙ ወንጀሎች

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ ወይም በአዋጁ መሰረት በወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች የተመለከቱትን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስፈርቶች፣ ሁኔታዎች ወይም ግዴታዎች ያልፈጸመ እንደሆነ እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ወይም እስከ ብር ፲፭ ሺ. በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

### 25. Certificate of Competency Related Offences

Any person failing to comply with the requirements, conditions or obligations of certificate of competency stated under this Proclamation or regulations or directives issued hereunder shall be punished with simple imprisonment up to three years or with a fine not more than Birr 15,000 or with both.

### ፳፮. በኤሌክትሪክ ተቋማት ላይ ጉዳት ስለማድረስ

በማመንጫ፣ ማስተላለፊያ ወይም ማከፋፈያ ተቋማት ላይ ጉዳት ያደረሰ ማንኛውም ሰው ከአምስት እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ወይም እስከ ብር ፶ሺ. በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

### 26. Damages on Electric Plants

Any person who causes damage to any generation transmission or distribution facility shall be punished with rigorous imprisonment from five up to fifteen years or with a fine of up to Birr 50,000 or with both.

### ፳፯. የባለሥልጣኑን ሥራ ስለማሰናከል

ማንኛውም የባለሥልጣኑ ተቆጣጣሪ በዚህ አዋጅ መሰረት ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ የተቃወመ፣ ያደናቀፈ፣ ችግር የፈጠረ ወይም በኢንስፔክተሩ በአግባቡ የተሰጠውን መመሪያ ሆን ብሎ ተላልፎ የተገኘ ማንኛውም ሰው ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም እስከ ብር ፳፭ሺ. በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

### 27. Obstruction of the Authority's Duty

Any person who resists, hinders or obstructs an inspector of the Authority acting pursuant to this Proclamation, or who intentionally fails to comply with any instructions duly given by the inspector shall be punished with simple imprisonment not exceeding five years or with a fine of up to Birr 25,000 or with both.

**፳፰. የኤሌክትሪክ ኃይል ስለመስረቅ**

ማንኛውም ሰው፡-

፩/ ማናቸውንም የኤሌክትሪክ ኃይል የሰረቀ፣ በሕገ-ወጥ መንገድ ከሌላ መስመር ጋር ያገናኘ፣ መስመሩን ያሰናከለ ወይም የኤሌክትሪክ ኃይል እንዲሰረቅ፣ ከሌላ መስመር ጋር እንዲገናኝ ወይም መስመሩ እንዲሰናከል ያደረገ፤ ወይም

፪/ መስመሩ የተሰረቀ፣ በሕገወጥ መንገድ ከሌላ መስመር ጋር የተገናኘ ወይም የተሰናከለ መሆኑን እያወቀ ከዚሁ መስመር ማናቸውንም የኤሌክትሪክ ኃይል ለፍጆታ ያዋለ ወይም የተገለገለ እንደሆነ፤

እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ወይም እስከ ብር ፳ሺ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

**፳፱. በኢነርጂ ላይ የሚፈጸሙ ሌሎች የወንጀል ጥፋቶች**

ማንኛውም ሰው፡-

፩/ በዚህ አዋጅ መሰረት በተሰጠ ፈቃድ ውስጥ የተመለከቱትን ማናቸውንም ሁኔታዎች የተላለፈ እንደሆነ፤

፪/ ከባለፈቃዱ ስምምነት ውጪ ባለፈቃዱ የኤሌክትሪክ ኃይል በሚያቀርብበት በማናቸውም የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት መስመር ላይ ማናቸውንም የኤሌክትሪክ አስተላላፊ ነገር ወይም የኤሌክትሪክ ዕቃ ያስቀመጠ፣ የተከለ ወይም የዘረጋ ወይም እንዲቀመጥ፣ እንዲተከል ወይም እንዲዘረጋ የፈቀደ እና ከዚሁ ጋር ያገናኘ ወይም እንዲገናኝ የፈቀደ እንደሆነ፤

፫/ በተከለለው የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ይዞታ ውስጥ የገነባ፣ ያረሰ ወይም የቆፈረ ወይም ሰብሎችን፣ አትክልቶችን ወይም ዛፎችን ያበቀለ ወይም የኤሌክትሪክ ግንባታ ወይም ሥራዎችን የሚያውኩ ወይም በኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽኖች ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ግንባታዎችን አላፈርስም፣ ዛፎችን አልቆርጥም ወይም አልመለምልም ወይም ሰብሎችን፣ አትክልቶችን ወይም ሌሎች ነገሮችን አላስወግድም ያለ እንደሆነ፤

፬/ በባለፈቃዱ የተገጠመለትን የኤሌክትሪክ ቆጣሪ ያሰናከለ ወይም እንዲሰናከል የፈቀደ ወይም የኤሌክትሪክ ፍጆታን እንዳይመዘግብ ያደረገ ወይም የተባበረ እንደሆነ፤

**28. Abstracting Electrical Energy**

Any person who:

1/ abstracts, unlawfully connect to other line, obstruct or cause to be abstracted, unlawfully connected to other lines or obstructed any electrical energy; or

2/ consumes or uses any electrical energy, knowing that it has been abstracted, unlawfully connected to other line or obstructed;

shall be punished with rigorous imprisonment of up to five years or with a fine of up to Birr 20,000 or with both.

**29. Other Electrical Energy Related Offences**

Any person who:

1/ violates any of the conditions of a license issued to him under this Proclamation;

2/ lays, erects or installs, or permits to be laid, erected or installed, any conductor or electrical equipment and connects it, or permits it to be connected, with any electric supply line through which electrical energy is supplied by a licensee, without the consent of the licensee;

3/ constructs, plows, digs, grows crops, plants or trees within the restricted areas of electrical installations or refuses to demolish any construction, cut or lop trees or to remove crops, plants or any other things that obstruct the construction or operation of electrical works or may cause danger to electrical installations;

4/ tampers, permits to be tampered or disables electrical meters installed by a licensee from recording electric consumption or gives assistance thereof;

፭/ ከባለፈቃዱ ስምምነት ውጪ ማናቸውንም ዓይነት የኤሌክትሪክ አስተላላፊ ነገሮችን ወይም የኤሌክትሪክ ዕቃዎችን የባለፈቃዱ ከሆኑት የኤሌክትሪክ አቅርቦት መስመሮች ላይ ያለያየ ወይም እንዲለያዩ የፈቀደ ወይም የተባበረ እንደሆነ፤

፮/ ከባለፈቃዱ በቅድሚያ የይሁንታ ማረጋገጫ ሳያገኝ በቋሚነት በተዘረጋለት የኤሌክትሪክ መስመር ላይ ማናቸውንም ለውጥ ያደረገ ወይም ለውጥ እንዲደረግበት የፈቀደ እንደሆነ፤

፯/ በማናቸውም መንገድ የኤሌክትሪክ ኃይል የአቅርቦት መጠኑ በሜትር ተለክቶ ሳይረጋገጥ ወይም ሊከፍልበት ከተዋዋለው ማናቸውም የኤሌክትሪክ እቃዎች ወይም መሣሪያዎች ውጪ የተጠቀመ ወይም እነዚህኑ የኤሌክትሪክ እቃዎች ወይም መሳሪያዎች ከተወሰነው ጊዜ እና ሊከፍልባቸው ከተዋዋለው ውጪ የተጠቀመባቸው እንደሆነ፤

፰/ የቀረበለትን የኤሌክትሪክ ኃይል ከቀረበበት ተግባር ውጪ ለሌላ ተግባር የተጠቀመ እንደሆነ፤

፱/ ከባለፈቃዱ ስምምነት ውጪ በባለፈቃዱ የተሰጠውን ማናቸውንም የኤሌክትሪክ ኃይል ለማንኛውም ሌላ ሰው የሰጠ እንደሆነ፤

፲/ ማናቸውንም የኤሌክትሪክ መስመር ተሸካሚ ምሰሶዎችን ወይም የተሸካሚ አካላትን ያለያየ ወይም የሰረቀ ወይም በመለያየቱ ወይም በስርቆቱ የተባበረ እንደሆነ፤ ወይም

፲፩/ በባለፈቃዱ ቁጥጥር ስር ባለ ማናቸውም ከኤሌክትሪክ ጋር ተያያዥነት ባለው ሥራ ላይ ሆን ብሎ ወይም በግድየለሽነት ጉዳት ያደረሰ ወይም ይህንኑ ያቋረጠ እንደሆነ፤

እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ወይም ከብር ፳፭ሺ ባልበለጠ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል::

## ፴. የኢነርጂ ብቃትን የሚመለከቱ ወንጀሎች

፩/ በዚህ አዋጅ ወይም በአዋጁ መሠረት በሚወጣው ደንብ መሠረት በተቀመጡት የኢነርጂ ብቃት አስገዳጅ ደረጃዎች የተመለከቱትን መስፈርቶች ያላሟላ ማናቸውንም ምርት ያመረተ፣ ወደ አገር ውስጥ ያስገባ፣ የተገበያየ፣ ያከፋፈለ ወይም የተጠቀመ ማንኛውም ሰው እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ እስራት ወይም እስከ ብር ፳፭ሺ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል::

5/ disconnects or permits to be disconnected any conductor or electrical equipment from any electric supply line belonging to a licensee, without the consent of the licensee;

6/ makes or permits to be made any alteration in his permanent installation without the previous approval of the licensee;

7/ uses electrical energy where the quantity of the supply of electrical energy is not ascertained by meter or uses any electrical equipments or device other than what he has contracted to pay for, or uses such electrical equipments or device at any other time than the time specified and for which he has contracted to pay;

8/ uses electrical energy supplied to him for purposes other than the purposes for which it is supplied;

9/ supplies to any other person any part of the electrical energy supplied to him by the licensee without the consent of the licensee;

10/ disconnects or abstracts any electric line towers or their parts or gives assistance thereto; or

11/ intentionally or negligently damages or breaks any works related to electricity under the control of a licensee;

shall be punished with up to five years rigorous imprisonment or with a fine not exceeding Birr 25,000 or with both.

## 30. Energy Efficiency Related Offences

1/ Any person, who manufactures, imports, trades, distributes or uses any product which does not meet the requirements specified in the energy efficiency mandatory standards fixed in accordance with this Proclamation or regulations issued hereunder shall be punished with up to five years rigorous imprisonment or with a fine not exceeding Birr 25,000 or with both.

፪/ ወንጀለኛው ደጋጋሚ ጥፋተኛ ሲሆን ወይም የተፈጸመው ወንጀል የአገርን ብሔራዊ ኢኮኖሚ በከፍተኛ ደረጃ የሚጎዳ ሲሆን ቅጣቱ እስከ አስር ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ወይም እስከ ብር ፩፻ሺ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ሊሆን ይችላል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ጥፋት ተፈጽሞባቸው የተገኙ የኢነርጂ ብቃት የሌላቸው ምርቶች በመንግስት ይወረሳሉ፡፡

## ፴፩. ሪፖርት ማድረግንና ሪከርድ መያዝን ስለመተላለፍ

ማንኛውም ሰው፡-

፩/ በዚህ አዋጅ ወይም በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች መሠረት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ የሚገባውን ሪፖርት ሳያቀርብ ከቀረ ወይም የተሳሳተ ሪፖርት ካቀረበ፤ ወይም

፪/ ባለሥልጣኑ በወሰነው ወይም ባጸደቀው ቅጽ እና አቀራረብ መሠረት መያዝ የሚገባውን ሪከርድ ሳይዝ ከቀረ፤

እስከ ሁለት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ወይም እስከ ብር ፲፭ሺ በሚደርስ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

## ፴፪. ሃሰተኛ ወይም አሳሳች መግለጫ ስለማቅረብ

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት መቅረብ የሚገባውን መረጃ በሚመለከት ሃሰተኛ ወይም አሳሳች መግለጫ ለባለሥልጣኑ ያቀረበ እንደሆነ እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ወይም እስከ ብር ፳፭ሺ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

## ፴፫. በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው አካል ላይ ስለሚጣል ቅጣት

በዚህ አዋጅ የተመለከቱት ወንጀሎች በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው ሰው በተፈጸመ ጊዜ ቅጣቱ አግባብ ያላቸውን የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች ተከትሎ ይወሰናል፡፡

2/ When the offender is a habitual offender or the offence damages the national economy of the country seriously, the penalty may extend up to fifteen years rigorous imprisonment or a fine of up to Birr 100,000 or with both.

3/ The energy inefficient products related to the commission of the offence referred to in sub-article (1) of this Article shall be forfeited to the government.

## 31. Reporting and Record Keeping Violations

Any person who:

1/ fails to make a report or files a false report to the Authority as required by this Proclamation or regulations or directives issued hereunder; or

2/ fails to keep records in the form and manner prescribed or approved by the Authority;

shall be punished with up to two years simple imprisonment or with a fine of up to Birr 15,000 or with both.

## 32. Presenting False or Misleading Statement

Any person who presents a false or misleading statement to the Authority in relation to any information required under this Proclamation shall be punished with simple imprisonment up to five years or with a fine of up to Birr 25,000 or with both.

## 33. Penalty on Juridical Persons

When an offence stated under this Proclamation is committed by a juridical person the penalty shall be determined in accordance with the relevant provisions of the Criminal Code.

## ክፍል ስምንት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፴፬. ክፍያዎች**

ማንኛውም ባለፈቃድ በዚህ አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ መሰረት ከተወሰነው ታሪፍ በላይ ክፍያ ሊጠይቅ አይችልም።

**፴፭. ስለከተማ ፕላን**

፩/ ማንኛውም የከተማ ፕላን የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ ሥርዓቱን በግልጽ መለየት እና ማሳየት ይኖርበታል።

፪/ ማንኛውም ባለፈቃድ የኤሌክትሪክ መስመር ሲዘረጋ የከተማውን ማስተር ፕላን ተከትሎ መሆን አለበት።

**፴፮. ስለሌሎች ግንባታዎች እና ሥራዎች**

ከኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ እና ማከፋፈያ ጣቢያዎች ወይም መስመሮች ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ወይም መመሪያ በሚወሰን የርቀት ክልል ውስጥ ማናቸውንም ዓይነት ግንባታዎች፣ እርሻዎች፣ ተክሎች ወይም ሌሎች የቋሚነት ጸባይ ያላቸውን ሥራዎች ማከናወን አይቻልም።

**፴፯. በነባር የማስተላለፊያ እና የማከፋፈያ መስመሮች ስለመጠቀም**

በባለፈቃዱ የማስተላለፊያ እና የማከፋፈያ መስመሮች ሌሎች ባለፈቃዶች የባለፈቃዱን ሥራዎች በማያደናቅፍ ሁኔታና ባለሥልጣኑ የሚወስነውን ታሪፍ በመክፈል እንዲገለገሉበት ሲጠይቁ መፍቀድ አለበት።

**፴፰. ስለክርክሮች አፈታት**

፩/ ባለሥልጣኑ፦

ሀ) ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ በሚደነገገው መሰረት ባለፈቃዱ ባላከበራቸው ከኤሌክትሪክ አገልግሎቶች ወይም ከኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ተግባራት ጋር በተገናኘ ደንበኛው በባለፈቃዱ የተመቻቸውን አቤቱታ የመስማት ሂደቶች በሙሉ ከፈፀመ በኋላ የሚቀርብለትን የደንበኛውን አቤቱታ መስማት አለበት፤

ለ) ከኤሌክትሪክ አቅርቦት ሁኔታዎች፣ ከታሪፍ ወይም ከአቅርቦት ወይም ከአገልግሎት ጥራት ጋር በተገናኘ በባለፈቃዶች መካከል ወይም በባለፈቃድና በደንበኛ መካከል አለመግባባት ሲከሰት እና ጉዳዩን ለባለሥልጣኑ ለማቅረብ ሲስማሙ ባለሥልጣኑ አለመግባባቱን በማስማማት ሊፈታው ወይም በግልግል ሊዳኘው ይችላል።

## PART EIGHT

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**34. Charges**

No licensee may claim charges in excess of the tariff set in accordance with this Proclamation and regulation issued hereunder.

**35. Town Plans**

1/ Any master plan of a town shall clearly demarcate and show the electrical distribution system layout thereof.

2/ Any licensee shall, while installing electrical lines, comply with the master plan of the town.

**36. Other Constructions and Works**

No construction, farming, plantation or any other activity of a permanent nature may be carried out within the clearance zone of electric transmission and distribution stations or lines to be set by regulations or directives to be issued hereunder.

**37. Access to Existing Transmission and Distribution Lines**

The licensee shall allow the use of his transmission and distribution lines to other licensees where their request is without impediment to his undertakings and they pay the tariff to be determined by the Authority.

**38. Settlement of Disputes**

1/ The Authority shall:

a) hear customer's complain for noncompliance related to electricity services or energy efficiency and conservation activities by a licensee, provided that the customer has exhausted all complaint hearing procedures arranged by the licensee in accordance with regulation to be issued hereunder;

b) mediate or arbitrate a dispute between licensees or between a licensee and a customer pertaining to the conditions of supply of electricity, tariff or quality of supply or provision of services, if they agree to submit it to the Authority.

፪/ ባለሥልጣኑ አለመግባባቱን በማስማማት ለመፍታት ቅድሚያ ይሰጣል፤ ሆኖም አለመግባባቱን በማስማማት ለመፍታት የማይቻል ከሆነ የመጨረሻና አስገዳጅነት ያለው ዳኝነት በመስጠት አለመግባባቱን በግልግል ይፈታል።

፫/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ለ) እና (፪) መሰረት አለመግባባቶችን በግልግል ለመፍታት እንዲችል የግልግል ፓናል ያቋቁማል።

፬/ የግልግል ፓናሉ አባላት እና በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚቀርቡ አለመግባባቶች እና አቤቱታዎች የሚፈቱበት ሥነ ሥርዓት በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

## ፴፱. ስለመክሰር

፩/ አግባብ ባላቸው የንግድ ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት በባለፈቃዱ ላይ የመክሰር ውሳኔ ከተሰጠና አዲስ ባለፈቃድ ሥራውን ለመቀጠል ፍላጎቱን ካሳየ የደንበኞችን ፍላጎት ከመጠበቅ አኳያ ባለሥልጣኑ የቀድሞውን ፈቃድ በመሰረዝ እና ማናቸውንም በቁጥጥሩ ስር ያሉ ተግባራትን ሁሉ በመፈጸም ሥራውን ወደ አዲሱ ባለፈቃድ ማስተላለፍ አለበት።

፪/ የቀድሞው ባለፈቃድ ሥራዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለአዲስ ባለፈቃድ ሲተላለፉ የቀድሞው ባለፈቃድ ንብረቶች በሙሉ ወይም በከፊል ወደአዲሱ ባለፈቃድ እንዲተላለፉለት ባለሥልጣኑ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር መተባበር አለበት።

## ፵. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።

፪/ ባለሥልጣኑ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የወጡ ደንቦችን በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

## ፵፩. የመመሪያዎች አወጣጥና ሕትመት

፩/ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵(፪) መሰረት ማንኛውንም መመሪያ ከማውጣቱ በፊት፦

ሀ) ባለፈቃዶችን፤

ለ) ከፍተኛ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን፤

ሐ) የኢነርጂ ብቃትን የሚተገብሩ ተቋማትን፤ እና

2/ In resolving the dispute the Authority shall give priority for mediation; provided, however, that if the dispute could not be resolved through mediation, arbitrate the dispute and render a final and binding award.

3/ In order to arbitrate disputes pursuant to sub-articles (1)(b) and (2) of this Article, the Authority shall form an arbitration panel.

4/ The members of the arbitration panel and the procedure to be followed for settlement of disputes and complaints under this Article shall be determined by regulation to be issued hereunder.

## 39. Bankruptcy

1/ When the licensee is declared bankrupt in accordance with the relevant provisions of the Commercial Code, and when a new licensee shows interest to continue the operation, the Authority shall revoke the previous license and do everything at its disposal to transfer the work to the new licensee with a view to safeguard the interests of customers.

2/ When a new licensee takes over the operations of the previous licensee pursuant to sub-article (1) of this Article, the Authority shall cooperate with the relevant bodies in order to effect the transfer of the assets of the previous licensee, partly or wholly, to the new licensee.

## 40. Power to Issue Regulation and Directive

1/ The Council of Ministers may issue regulations necessary for the proper implementation of this Proclamation.

2/ The Authority may issue directives necessary for the proper implementation of this Proclamation and regulations issued under sub-article (1) of this Article.

## 41. Issuance and Publication of Directives

1/ The Authority shall, before issuing any directive under Article 40(2) of this Proclamation, consult such persons as appears to it to be representatives of:

a) licensees;

b) users of bulk electricity services;

c) energy efficiency implementing entities; and

መ) ሌሎች ባለድርሻዎችን፣

ሊወክሉ ይችላሉ ብሎ የሚገምታቸውን ሰዎች ማማከር አለበት።

፪/ ባለሥልጣኑ የሚያወጣቸውን መመሪያዎች የማሳተም ሃላፊነት አለበት።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ማናቸውም መመሪያ ስለሚታተምበት አግባብ በባለሥልጣኑ ይወሰናል።

**፵፪. <u>የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸዉ ሕጎች</u>**

፩/ የኤሌክትሪክ አዋጅ ቁጥር ፹፮/፲፱፻፹፱ በዚህ አዋጅ ተሽሯል።

፪/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

**፵፫. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>**

፩/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፪(፩) ድንጋጌ ቢኖርም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ መሠረት የሚወጣው ደንብ እስከሚጸናበት ቀን ድረስ በኤሌክትሪክ አዋጅ ቁጥር ፹፮/፲፱፻፹፱ ተቋቁሞ የነበረው የኤሌክትሪክ ኤጀንሲ ሕጋዊ ሰውነቱን እንደያዘ በመቀጠል በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል።

፪/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፪(፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በኤሌክትሪክ አዋጅ ቁጥር ፹፮/፲፱፻፹፱ መሰረት ወጥተው የነበሩ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ስታንዳርዶች በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጡ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ስታንዳርዶች እስከሚተኩ ድረስ ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል።

፫/ በኤሌክትሪክ አዋጅ ቁጥር ፹፮/፲፱፻፹፱ እና በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦችና መመሪያች መሰረት ተሰጥተው የነበሩ ፈቃዶችና የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቶች በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት እንደተሰጡ ይቆጠራል።

**፵፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥር ፲፱ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

d) other stakeholders.

2/ The Authority shall have the duty to publish the directives it issues.

3/ The manner of publication of any directive under sub-article (2) of this Article shall be determined by the Authority.

**42. <u>Repealed and Inapplicable Laws</u>**

1/ The Electricity Proclamation No.86/1997 is hereby repealed.

2/ No law or practice may, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, be applicable with respect to matters provided for by this Proclamation.

**43. <u>Transitory Provisions</u>**

1/ Notwithstanding the provisions of Article 42(1) of this Proclamation, the Electricity Agency established under Proclamation No.86/1997 shall retain its legal personality and exercise the powers and duties given to the Authority by this Proclamation until the effective date of the regulation to be issued pursuant to Article 3 of this Proclamation.

2/ Without prejudice to the provisions of Article 42(2) of this Proclamation, regulations, directives and standards issued pursuant to the Electricity Proclamation No. 86/1997 shall remain in force until replaced by regulations, directives and standards issued hereunder.

3/ Licenses and certificates of competency issued pursuant to the Electricity Proclamation No. 86/1997 and regulations and directives issued thereunder shall be deemed to be issued pursuant to this Proclamation and regulations and directives issued hereunder.

**44. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 27th day of January, 2014.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**